# በኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጋብቻዎች ፡ መፍረስ ፤

## ከኖርማን ፡ ጂ ፡ ሲንገር ።*

በሸዋን ፡ ግዛው ፡ እንግዳ ፡ ወርቅ ፤ ከሳሽ ፡ ንጋቱ ፡ ይመር ፡ ተከሳሽ[1] ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ በጣም ፡ ስለሚጠበቡበት ፡ ፕሮብሌም ፡ (ችግር) ፡ የተመለከተ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በጠቅላላው ፡ ለሕግ ፡ ቅንጅቶች ፡ እድገት ፡ ጠቃሚነት ፡ ያለው ፡ ነው ። ይህ ፡ ፍርድ ፡ እንደ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በታወጀ ፡ ሕግና ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ የሚያትታቸውን ፡ አንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ ይዞ ፡ በነበረው ፡ በሃይማኖት ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ ይመለከታል ፤ ማለት ፡ አዲሱ ፡ ሕግ ፡ የሃይማኖቱን ፡ ሕግ ፡ የሚተካ ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ የሚሆነው ፡ እንዴት ፡ ነው?

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ሁኔታ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ የክርስቲያን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ[2] ፡ መሠረቱ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ነበር[3] ። ይህም ፡ ሕግ ፡ ሃይማኖታዊና ፡ ዓለማዊ ፡ ሲሆን ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ሃይማኖታዊው ፡ ነክ ፡ ነበር ። ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሠረት ፡ የተፈጸሙን ፡ ጋብቻዎች ፡ ቅዱስነት ፡ ለይቶ ፡ ይናገራል ። ማንኛውም ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጋብቻን ፡ የፈጸመ ፡ ክርስቲያን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እምነት ፡ እንደ ፡ ታወቀውና ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥትም ፡ ውስጥ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ጋብቻን ፡ ማፍረስ ፡ የሚቻለው[4] ፡ በጣም ፡ በተወሰኑ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሲሆን ፡ ለነዚህም ፡ በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ ሲኖሩ ፡ እንደነበር ፡ ያውቅ ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ አሉ ፡ የሉም ፡ የሚሉትና ፡ ጋብቻው ፡ ሊፈርስ ፡ መቻሉን ፡ ሊወስኑ ፡ የሚችሉት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ብቻ ፡ መሆናቸውን ፡ ያውቅ ፡ ነበር ። የሕዝብ ፡ (የሲቢል) ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ ሥልጣን ፡ አልነበራቸውም ።

---

* የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩሊቲ ።

1. የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፫ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፶፱) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፸፱ ።
2. አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፻፷፭/፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በተለይ ፡ የወጣ ።
3. የሎውንስታይንን ፡ "የኢትዮጵያ ፡ የወንጀል ፡ እቅድ ፡ (ቅንጅት)" ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፪ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፶፰) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፶፩ ፡ ይመለከቷል ። ግራቨን ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ" ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፩ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፶፯) ገጽ ፡ ፪፻፺፯ ።
4. ምዕራፍ ፡ ፳፬ ፡ ክፍል ፡ ፯ ። ሲፈርስ ፡ ለሚችል ፡ ጋብቻ ፡ (የእንግሊዝኛው ፡ ትርጉም ፡ ከአባ ፡ ጳውሎስ ፡ ጻድዋ ፡ የተዘጋጀው ፡ በፕሮፌሰር ፡ ፒተር ፡ ስትራውስ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩንቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ተጠባባቂነት ፡ ፲፱፻፶፱) ፡ የተጠቀሱት ፡ ምክንያቶች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

   ፩) ባልና ፡ ሚስት ፡ መንፈሳዊ ፡ ኑሮ ፡ ለመኖር ፡ ከመረጡ ።

   ፪) ከባልና ፡ ሚስት ፡ አንደኛው ፡ ግንኙነት ፡ አናደርግም ፡ ካሉ ።

   ፫) እርስ ፡ በርስ ፡ መረዳዳትና ፡ መተጋገዝ ፡ የሌለበት ፡ ጋብቻ ፡ ማለት ፤

      ሀ) የዝሙት ፡ ተግባር ፡ ሲፈጸሙ ።

      ለ) ከባልና ፡ ሚስት ፡ በአንደኛው ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ሲደርስ ።

ሆኖም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ይታወቅ ፡ የነበረው ፡ ጋብቻ ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብቻ ፡ ብቻ ፡ አልነበረም ። አንድ ፡ ሰው ፡ የአገርን ፡ ልማድ ፡ በመቀበል ፡ (የልማድ ፡ ጋብቻ) ፡ የሌላ ፡ ሃይማኖት ፡ ሥርዓቶችን ፡ በመከተል ፡ ወይም ፡ ደንበኛ ፡ የቀበሌው ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ በመንግሥት ፡ ስም ፡ ጋብቻውን ፡ እንዲያጸድቅለት ፡ በማድረግ ፡ (ብሔራዊ ፡ ጋብቻ) ፡ ጋብቻ ፡ ሊፈጽም ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ የእንዚህ ፡ ጋብቻዎች ፡ መፍረስ ፡ እንዲቋቋሙ ፡ በረዱት ፡ ልምዶች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነበር ።

ጋብቻን ፡ ከሚመለከቱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ውስጥ ፡ የበለጠ ፡ ዘላቂነት ፡ ካላቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ "የልማድ" [5] ፡ ሕጎች ፡ የተወሰዱ ፡ ይገኛሉ ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ አላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ሦስቱንም ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ ተቀብሏቸዋል [6] ፤ ለማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻዎች [7] ፡ የሚሆኑ ፡ አጠቃላይ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ዘርዝሯቸዋል ፤ እንዲሁም ፡ የጋብቻዎችን ፡ መፍረስ [8] ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ ይዟል ።

ስለ ፡ ጋብቻዎች ፡ መፍረስ ፡ የተመለከተው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ድርጅቶችና ፡ ደንቦች ፡ የወደፊት ፡ አቋም ፡ ተቃራኒ ፡ ሊመስሉ ፡ የሚችሉ ፡ መሠረታዊ ፡ አሳቦችን ፡ ይዟል ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፭፻፸፮ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

---

5. ቍጥር ፡ ፯፻፳፭-፯፻፴፯ን ፡ እና ፡ ፯፻፳፪-፯፻፳፬ ፡ ይመለከቷል ። እነዚህ ፡ ቍጥሮች ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የሚናገሩ ፡ ናቸው ። የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ በኢትዮጵያ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የጠነከረ ፡ አቋም ፡ ነበራቸው ፤ እነሱም ፡ "ሽማግሌዎች" ፡ በሚል ፡ ስም ፡ የታወቁ ፡ ሲሆኑ ፡ በተለይ ፡ በእድሜ ፡ ገፋ ፡ ያሉና ፡ ስለ ፡ ግል ፡ አቋም ፡ የሚሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደ[ሴ]ት ፡ እንደሚቆረጡ ፡ የሚያውቁ ፡ ነበሩ ።

6. ዳቪድ ፡ ሰ ፡ ድርዋ ፡ ዴ ፡ ላ ፡ ፋሚል ፡ ን ፡ ላ ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ኢቶፒ ፡ (፲፱፻፷፯) ፡ ገጽ ፡ ፰ ።

<u>ቍጥር ፡ ፭፻፸፯ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻ ፤</u>

፩) ጋብቻ ፡ ባንድ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ፊት ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

፪) እንደዚሁም ፡ ሕጉ ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ ባገር ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ የሚደረጉትን ፡ ጋብቻዎች ፡ ያውቃል ፡ (ይቀበላል) ።

<u>ቍጥር ፡ ፭፻፸፰ ። ብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፤</u>

ጋብቻ ፡ ለማድረግ ፡ አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ በክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ፊት ፡ ሲቀርቡና ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹምም ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ሲቀበለው ፡ ጋብቻ ፡ ተፈጸመ ፡ ይባላል ።

<u>ቍጥር ፡ ፭፻፸፱ ። የሃይማኖት ፡ ጋብቻ ፤</u>

አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ውሳኔዎችን ፡ ወይም ፡ ሥርዐቶችን ፡ እንደ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ባንደኛው ፡ ሃይማኖት ፡ ሲፈጽሙ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ የሚጸና ፡ ጋብቻ ፡ እንዳቋቋሙ ፡ ይቆጠራል ።

<u>ቍጥር ፡ ፭፻፹ ። የልማድ ፡ ጋብቻ ፤</u>

አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ በጐሣቸው ፡ ልማድ ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ በአንደኛው ፡ ጐሣ ፡ ልማድ ፡ ከሁለቱ ፡ መካከል ፡ ነዋሪ ፡ የሆነውን ፡ ግንኙነት ፡ የሚያስከትል ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ ፈጽመዋል ፡ የሚያሰኘውን ፡ ካደረጉ ፡ በመካከላቸው ፡ ጋብቻ ፡ አለ ፡ ይባላል ።

7. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ፭፻፹፩-፭፻፺፬ ። እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ስለ ፡ ዕድሜ ፡ ዝምድና ፡ (የሥጋ ፡ ዝምድና ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና) ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ እና ፡ ስለ ፡ ሌሎችም ፡ ይናገራሉ ።

“እንዲሁም ፡ በሃይማኖት ፡ ሥርዓት ፡ የተፈጸመ ፡ ጋብቻ ፡ በሃይማኖት ፡ ባለ ሥልጣኖች ፡ የማይጸና ፡ መሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፡ የዚሁኑ ፡ ጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ የሚያስከትል ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ አለ ፡ ለማለት ፡ ይቻላል” ።

ይህ ፡ ቍጥር ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብቻን ፡ መፍረስ ፡ ጉዳይ ፡ መወሰን ፡ ያለባቸው ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖቹ ፡ ናቸው ፤ እነሱም ፡ በሃይማኖት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ውሳኔያቸውን ፡ ሊሰጡ ፡ ይችላሉ ፡ የሚል ፡ ትርጉምን ፡ ይሰጣል ፡ ይባል ፡ ይሆናል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፳፪ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡

(፩) የጋብቻው ፡ ሥርዓት ፡ የተፈጸመበት ፡ ሥርዓት ፡ ማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፡ የጋብቻው ፡ መፍረስና ፡ ይህ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

(፪) ጋብቻው ፡ የተፈጸመው ፡ በአንድ ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ ፊት ፡ ወይም ፡ በሃይማኖት ፡ ሥርዐት ፡ ወይም ፡ በአገር ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ቢሆን ፡ በጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ረገድ ፡ ማንኛውም ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ አይደረግም ።

ይህ ፡ ቍጥር ፡ ለብቻው ፡ ሲነበብ ፡ የጋብቻ ፡ ማፍረስ ፡ ጉዳይ ፡ ሲነሳ ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ምንም ፡ ሥልጣን ፡ የላቸውም ፡ የሚል ፡ ይመስላል ። በተጨማሪም ፡ አንድ ፡ ያገባ ፡ ሰው ፡ ጋብቻው ፡ ምንም ፡ አይነት ፡ ይሁን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በተጠቀሱት ፡ ጋብቻ ፡ ማፍረሻ ፡ ምክንያቶችና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ ሊጠቀም ፡ ይችላል ፤ የሚል ፡ ይመስላል ። እነዚህ ፡ ምክንያቶችና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ ለምሳሌ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን [9] ፡ ከምትፈጽመው ፡ በላይ ፡ ጋብቻዎችን ፡ ወደ ፡ ማፍረስ ፡ ይመራሉ ።

የሸዋን ፡ ግዛው ፡ እንግዳወርቅ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ሲታይ ፡ በእነዚህ ፡ ደንቦች ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ መስሎ ፡ የሚታየው ፡ ተቃራኒነት ፡ በጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ ተደቅኖ ፡ ነበር ። አቤት ፡ ባይዋ ፡ ጋብቻዋ ፡ እንዲፈርስ ፡ ስትል ፡ ከከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት [10] ፡ አቤቱታዋን ፡ አቀረበች ። ክርክር ፡ ከቀረበባቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከወረራው ፡ በፊት ፡ የተፈጸመው ፡ ጋብቻ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓቶችን ፡ የተከተለ ፡ መሆኑን ፡ አረጋገጠ ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በአስተያየት ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ጉዳይ ፡ ለመመልከት ፡ ሥልጣን ፡ ወዳላቸው ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ ሴትዮዋ ፡ መሄድ ፡ አለባት ፡ ብሎ ፡ ወሰነ ። ለመፋታት ፡ የሚቻለው ፡ እነኝህ ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ በቂ ፡ መንፈሳዊ ፡ ምክንያ

8. ቍጥር ፡ ፯፻፳፪(፩) ።

የጋብቻው ፡ ሥርዓት ፡ የተፈጸመበት ፡ ሥርዓት ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ቢሆን ፡ የጋብቻው ፡ መፍረስና ፡ ይህ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ነው ።

9. ሆኖም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋብቻውን ፡ ለማፍረስ ፡ ትችላለች ፡ ስለዚህም ፡ አንዳንድ ፡ ምክንያቶችን ፡ ትሰጣለች ።

10. ይግባኝ ፡ ባይዋ ፡ በቍ ፡ ፯፻፸፱–፯፻፹፪ ፡ መሠረት ፡ ጉዳይዋን ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ፊት ፡ ማቅረብ ፡ የነበረባት ፡ ይመስል ፡ ነበር ፡ ሆኖም ፡ ይግባኝ ፡ ባይዋ ፡ ጥያቄዋን ፡ ወዲያው ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀረበችበት ፡ ምክንያት ፡ ለመፋታት ፡ የምታቀርበውን ፡ ጥያቄ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የት ፡ ማቅረብ ፡ እንዳለባት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይመስላል ።

ቶች ፡ ሲያገኙ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የከፍተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲያጸድቅ ፣ አንድ ፡ ዳኛ ፡ ከፍርዱ ፡ በሐሳብ ፡ ተለይተዋል ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀረበለትን ፡ ጉዳይ ፡ በደንብ ፡ ከማብራራት ፡ አልፎ ፡ ተርፎ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ከሁን ፡ በፊት ፡ ግን ፡ በሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሥልጣን ፡ ስር ፡ የነበሩት ፡ ጉዳዮች ፡ አሁን ፡ የሚተዳደሩት ፡ በየትኛው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ ተመልክቷል ። የሃይማኖት ፡ ጋብቻን ፡ ለማፍረስ ፡ ክስ ፡ ሲቀርብ ፡ ጉዳዩ ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፸፮ ፡ ስር ፡ ይመጣል ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ወሰነ ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠው ፡ ትርጉም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በመጀመሪያ ፡ የተጠቀሰው ፡ ሲሆን ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፡ አንድ ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብቻን ፡ የፈጸመ ፡ ሰው ፡ ጋብቻውን ፡ ለማፍረስ ፡ ሲፈልግ ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፸፮ ፡ መሠረት ፡ ጉዳዩን ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ ወስዶ ፡ በሃይማኖት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ጋብቻውን ፡ ማፍረስ ፡ መቻል ፡ አለመቻሉን ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

በዚህ ፡ አተረጓጐም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓቶች ፡ መሠረት ፡ ያገባችው ፡ ወይዘሮ ፡ ሽዋን ፡ ግዛው ፡ ጋብቻዋ ፡ ይፈርስ ፡ ዘንድ ፡ ለሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ማመልከት ፡ አስፈለጋት ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፸፮ ፡ መሠረት ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ በምትመርጠው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ ጋብቻውን ፡ ለማፍረስ ፡ ወይም ፡ ለመፋታት ፡ የምትችለው ፡ መጀመሪያ ፡ ይህንን ፡ ስታደርግ ፡ ብቻ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዓይነት ፣ ቍጥር ፡ ፲፻፸፮ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ይሠራባቸው ፡ የነበሩትን ፡ የሃይማኖት ፡ ደንቦች ፡ እንዳሉ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በማግባትና ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብቻዎችን ፡ ለማፍረስ ፡ የሚቻለው ፡ በእነርሱ ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ፡ በማድረግ ፡ ተተርጉሟል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ የሰጠው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣንን ፡ በማስታከክ ፡ ሲሆን ፣ አንድ ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብቻን ፡ የማፍረስ ፡ ጉዳይ ፡ መጀመሪያ ፡ መቅረብ ፡ ያለበት ፡ ከከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይልቅ ፡ ለሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለቤተ ፡ ክህነት ፡ ጉቤኤ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ወሰነ ።

የመሀሉ ፡ ዳኛ ፡ በሰጡት ፡ የተለየ ፡ የፍርድ ፡ አስተያየት ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ የቀድሞው ፡ ሕግ ፡ ምንም ፡ ይሁን ፡ በሳቸው ፡ አስተያየት ፡ ለጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ ወዳላቸው ፡ ቍጥር ፡ ፲፻፸፯ና ፡ የሚከተሉት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቍጥሮች ፡ መሄድ ፡ አለብን ፡ ሲሉ ፡ ተከራክረዋል [11] ። እሳቸውም ፡ አስተያየታቸውን ፡ የመሠረቱት ፡ "በዳኝነት ፡ ሥልጣን" ፡ ጽንስ ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ ቢሆንም ፣ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፸፪ ፡ ላይ ፡ በይበልጥ ፡ የተመሠረተው ፡ ውሳኔያቸው ፡ ስለ ፡ ጋብቻን ፡ መፍረስ ፡ የሚነሱትን ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳዮች ፡ ለመወሰን ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ የሚል ፡ ነበር ። ስለ ፡ ጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ የሚነሱት ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳዮች ፡ የሚወሰኑት ፡ በሃይማኖት ፡ ደንቦች ፡ ሳይሆን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ውሳኔያቸው ፡ ብዙዎችን ፡ ቅር ፡ ያሰኝ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ በማሰብ ፡ ውሳኔያቸውን ፡ እንዲሰጡ ፡ ያስገደዳቸው ፡ ሕጉ ፡ እንጂ ፡ የእርሳቸው ፡ የግል ፡ ፍላጐት ፡ አለመሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ ደከመዋል ።

---

11. ቍጥር ፡ ፲፻፸፫ ፡ እና ፡ የሚለጥቁት ፡ ቍጥሮች ፡ ስለ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ሥራ ፡ እና ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ጋብቻ ፡ ለማፍረስ ፡ መከተል ፡ ስለሚገባው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይናገራሉ ።

በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳዮች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣ ንን ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ። በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የተሰጠው ፡ የፍርድ ፡ አስተ ያየት ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ለሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ እን ደሚሰጥ ፡ ያመለክታል [12] ። ሆኖም ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ እና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሁለቱም ፡ የጋብቻን ፡ መፍረስ ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚመለከቱ ፡ የሃይማኖት ፡ ባለ ሥልጣኖች ፡ አሁንም ፡ ለዓለማዊ ፡ ጉዳዮች ፡ ጋብቻን ፡ ለማፍረስ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ በአሳብ ፡ የተለዩት ፡ ዳኛ ፡ መሆን ፡ አለመሆኑ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። ውሳኔም ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥትን ፡ ይጠቅሳል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የጠቀ ሰው ፡ በዳኛው ፡ አስተያየት ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በጋብቻ ፡ ማፍረስ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የተወሰነ ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ ነው ። በአሳብ ፡ በተለዩት ፡ ዳኛ ፡ አስተያየት ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሥልጣን ፡ ሊኖራቸው ፡ የሚችለው ፡ አንድ ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳይ ፡ ሃይማኖት ፡ ነክ ፡ ሲሆን ፡ ለምሳሌ ፡ የሃይማኖት ፡ ደንብ ፡ የሚከለክለው ፡ ጋብቻ ፡ ሲፈጸም ፡ ብቻ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህም ፡ ቢሆን ፡ እንኳን ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጋብ ቻውን ፡ ሊያፈርሱ ፡ የሚችሉት ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (ለመንፈሳዊ) ፡ ጉዳዮች ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ጋብቻው ፡ ለሥጋዊ ፡ (ለሲቢል) ፡ ጉዳዮች ፡ እንዲፈርስ ፡ ከተፈለገ ፡ ጉዳዩ ፡ በዓለማዊ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መታየት ፡ አለበት ። የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣ ኖች ፡ ጋብቻውን ፡ ካፈረሱት ፡ ይህ ፡ አድራጐታቸው ፡ የባልና ፡ ሚስቶቹን ፡ መፋ ታት ፡ እንደሚያስከትል ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ተቆጥሮ [13] ፡ በፍጥነት ፡ እርምጃ ፡ ይወሰድበታል [14] ። ሆኖም ፡ አንድ ፡ አመልካች ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ ሲል ፡ ሌላ ፡ አጥጋቢ ፡ ምክንያት ፡ ካቀረበ ፡ ጋብቻው ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብቻ ፡ ቢሆንም ፡ ከሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጋብቻው ፡ የፈረሰ ፡ መሆኑን ፡ የሚያሳይ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲያመጣ ፡ አይገደድም ።

በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ውሳኔ ፡ የሰጡት ፡ ዳኞች ፡ "ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምእመ ናንን ፡ በንስሐ ፡ የምትሠራበት ፡ የምትቀጣበት ፡ የግል ፡ ዳኝነት" ፡ ያላት ፡ መሆ ኑን ፡ ለማሳየት ፡ በቍጥር ፡ ፪—፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሰጠውን ፡ ድንጋጌ ፡ ፲ኛ ፡ አንቀጽ [15] ፡ ጠቅሰዋል ። እነሱም ፡ ይህን ፡ አንቀጽ ፡ አንድ ፡ ክርክር ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያንን ፡ የሚጠቅስ ፡ (የሚነካ) ፡ ከሆነ ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ማንም ፡ ሊጋራቸው ፡ የማይችል ፡ የግል ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ፤ ይላል ፡ ብለው ፡ ተርጉመውታል ። ነገር ፡ ግን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ "በዓለማዊ ፡ ዳኝነት ፡ የመን ግሥቱ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ያስተዳድራሉ" ፡ የሚለውን ፡ የዚህን ፡ አንቀጽ ፡ ክፍል፡ ሳይተረጉሙ ፡ ቀርተዋል ። በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ውሳኔ ፡ የሰጡት ፡ ዳኞች ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ለሌሎች ፡ በእርግጥ ፡ ዓለማዊ ፡ ሆነው ፡ መንፈሳዊ ፡ ነገሮችንም ፡ ለያዙ ፡

---

12. የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፫ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፶፱) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፹፮ ።

13. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፮፻፹፩ ።

14. የጋብቻውን ፡ መፍረስ ፡ የሚያስከትል ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ሲኖር ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የመፋታት ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ የምበት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ አላቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መፋታት ፡ የሚወሰንበት ፡ ምክንያት ፡ "ከባድ" ፡ ሳይሆን ፡ "ሌላ ፡ ምክንያት" ፡ ከሆነ ፡ የሽምግ ልና ፡ ዳኞች ፡ እርምጃ ፡ ከመውሰዳቸው ፡ በፊት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ሊወስዱ ፡ ይችላሉ ።

15. ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደንብ ፡ በቍጥር ፡ ፪ ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሰጠው ፡ ድንጋጌ ፡ ፲ኛ ፡ አንቀጽ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ኅዳር ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ። ይህ ፡ አንቀጽ ፡ እርእሱ ፡ "ስለ ፡ ዳኝነት" ፡ የሚል ፡ ሲሆን ፡ በምእመናን ፡ ላይ ፡ "የግል" ፡ ዳኝነት ፡ አለ ፡ ይላል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ንን ፡ ዳኝነት ፡ ከ"ዓለማዊ ፡ ዳኝነት" ፡ ለይቶታል ።

ክርክሮች ፡ "ለዓለማዊ ፡ ዳኝነት ፡ የሚበቁ ፡ ሰዎች ፡ የመንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ። የሚሾሙትም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ነው" ቢባልም ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ንባብ ፡ የሚመለከት ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ ንባቡን ፡ ውድቅ ፡ አድርገውታል ።

ይህ ፡ በመጨረሻ ፡ የተጠቀሰው ፡ ንባብ ፡ ብቻውን ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ውሳኔ ፡ የሰ ጉትን ፡ ዳኞች ፡ ክርክር ፡ የሚያፈርስባቸው ፡ ይመስላል ። ይህ ፡ ንባብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ስር ፡ ለሚነሱት ፡ አንዳንድ ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳዮች ፡ በመንግሥት ፡ የተቋቋመው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዋናውን ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የያዘ ፡ ሆኖ ፡ ግን ፡ የሕጉን ፡ መንፈሳዊ ፡ ምንጮች ፡ በተለይ ፡ ማወቅ ፡ በጣም ፡ አግባብ ፡ የሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የመንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ ይህንን ፡ የተለየ ፡ እውቀት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲያውሉ ፡ ለዳኝነት ፡ የሚበቁ ፡ ሰዎች ፡ ማቅረብ ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ጉዳዩ ፡ የሚወሰነው ፡ በዓለማዊ ፡ ሕግና ፡ በዓለማዊ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ነው ፤ የሚል ፡ ይመስላል ። ፲ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የነበራትን ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ በማንሳት ፡ ግርማዊነታቸው ፡ በፋሺስት ፡ ወረራ ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ ሀገር ፡ ሄደው ፡ ከስደት ፡ ሲመለሱ ፡ ከተጀመረው ፡ ጠቅላላ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ መሻሻል ፡ አንዱ ፡ ሆኗል ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አብዛኛውን ፡ የድሮ ፡ ሥልጣኗን ፡ ያጣችው ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ ከተጀመረው ፡ መሻሻል ፡ አንስቶ ፡ ባ፲፱፻፶፭ ፡ ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሲታወጅ ፡ ከዚያም ፡ ቀጥሎ ፡ የቀሩት ፡ ሕጎች ፡ ከወጡ ፡ በኋላና ፡ እስካሁን ፡ ድረስ [16] ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የሥልጣን ፡ ማንሳት ፡ ጉዳይ ፡ ነጠላውን ፡ ዋንኛ ፡ የሚመስለው ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ፲ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ይህ ፡ አንቀጽ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ለምን ፡ ዓይነት ፡ ጉዳይ ፡ መዋሉን ፡ (ማገልገሉን) ፡ ብቻ ፡ ቢመረምርም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ይህ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ከመወሰኑ ፡ በፊት ፡ ይህንን ፡ አንቀጽ ፡ በነጠላ ፡ ፍቺው ፡ ሲጠቀሙበት ፡ እንደቆዩ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንፈሳዊ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ አላት ፡ ሲባል ፡ እንደ ፡ ጾም ፡ ጸሎት ፡ ሱባኤ ፡ ባሉት [17] ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅጣቶች ፡ ልትቀጣቸው ፡ ለምትችለው ፡ በተፈጥሮ ፡ መንፈሳዊ ፡ ለሆኑት ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ይመስላል ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አነስተኛው ፡ ሃይማኖት ፡ እስላም ፡ በተለይ ፡ በሕግ ፡ ስለታወቀ ፡ መሠረታዊው ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳይ ፡ የተወሳሰበ ፡ ሆኗል ። በእስላሞች ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ የግል ፡ ግንኙነቶች ፡ የሚፈጥሯቸውን ፡ ክርክሮች ፡ የሚቀበሉ ፡ የተለዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ተቋቁመዋል [18] ። የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ ዜጎች ፡

---

16. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (፲፱፻፵፱) ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ (፲፱፻፶፪) ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ (፲፱፻፶፫) ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ (፲፱፻፶፪) ፡ የባሕር ፡ ሕግ ፡ (፲፱፻፶፪) ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ (፲፱፻፶፰) ፡ አሁን ፡ በመዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የማስረጃ ፡ ሕግ ።

17. የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፫ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፶፰) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፶፩ ። ይህ ፡ በአሳብ ፡ በተለዩት ፡ ዳኛ ፡ አስተያየት ፡ ነው ።

18. የቃዲዎችና ፡ የናኤባዎች ፡ ጉባኤ ፡ ቤት ፡ የተቋቋመበት ፡ በቍጥር ፡ ፷፪ ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ግንቦት ፡ ፳፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጣል ፡ (ያቋቁማል) ።

(ሀ) የጋብቻ ፤ የመፋታት ፡ የመኖሪያ ፡ ገንዘብ ፡ ለሕግ ፡ ያልበቁ ፡ ሕጻናት ፡ ሞግዚትነትና ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፡ በተዘምዶ ፡ ጉዳይ ፡ የተነሣ ፡ ጋብቻ ፡ እንደ ፡ እስላም ፡ ሕግ ፡ የተፈጸመ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤ ወይም ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ሁሉም ፡ እስላሞች ፡ የሆኑ ፡ እንደሆነ ።

በሆኑት ፣ እስላሞች ፣ ቍጥር ፣ ምክንያት ፣ የተለዩት ፣ የእስላም ፣ ደንቦች ፣ በኢት ዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተጨምረዋል ። በሸዋን ፡ ግዛው ፡ የፍርድ ፣ ጉዳይ ፣ ውስጥ ፡ በድምጽ ፣ ብልጫ ፣ ውሳኔ ፡ የሰጡት ፣ ዳኞች ፣ ሲከራከሩ ፣ እስላሞች ፣ በተለዩ ፡ ሃይማኖት ፣ ነክ ፣ በሆኑ ፣ ደንቦች ፣ እንዲጠቀሙ ፣ ስለተፈቀደላቸው ፣ ክርስቲያኖችም ፣ እንደዚሁ ፣ ለእስላሞች ፡ በተፈቀደላቸው ፡ ልክ ፡ የሕግ ፣ ነክ ፡ ጉዳይ ፣ ሲገጥሟቸው ፣ በራሳቸው ፡ መንፈሳዊ ፣ ደንቦች ፣ እንዲጠቀሙ ፣ ሊፈቀድላቸው ፡ ይገባል ፣ ብለዋል ። ነገር ፣ ግን ፣ በሁለቱ ፣ ሃይማኖቶች ፣ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አይደ ረግ ፣ የሚለው ፣ የፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ክርክር ፣ ልክ ፣ ሊሆን ፡ ሲችል ፣ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ውሳኔ ፣ የማይደግፍ ፣ ሊሆን ፡ ይችላል ። የተመለከትናቸው ፡ ቍጥሮች ፡ ስለ ፣ ሃይ ማኖት ፡ ጋብቻዎች ፣ የሚናገሩት ፡ አንዱን ፣ ካንዱ ፡ ባለመለየት ፡ ነው ። እነዚሁ ፣ ቍጥሮች ፡ የኢትዮጵያ ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖትን ፣ የእስላም ፣ ሃይማኖትን ፡ ወይም ፣ ሌላ ፣ ሃይማኖትን ፣ ለይተው ፣ አይጠቅሱም ። በዚህ ፣ ዓይነት ፣ ምናል ባት ፡ የፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ሕግ ፣ በሁሉም ፣ ሃይማኖቶች ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፣ አያደ ርግም ። ይህም ፡ ሲባል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፣ ሃይማኖት ፣ ልማዶች ፡ የደነገገው ፣ ደንብ ፣ በድምጽ ፣ ብልጫ ፣ ውሳኔ ፣ የሰጡት ፣ ዳኞች ፣ የመረጡት ፡ የሃይማኖት ፣ ጋብቻዎች ፣ የሚፈርሱት ፣ በሃይማኖታዊ ፣ ምክንያቶችና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ ብቻ ፣ ነው ፣ የሚለውን ፣ ነው ፡ ማለታችን ፣ አይደለም ። አነስተኛ ፡ ድምጽ ፣ የሰጡት ፡ ዳኛ ፣ እንደተከራከሩት ፡ ሁሉ ፣ ማንኛውም ፡ ሰው ፣ ሃይማኖቱ ፡ ምንም ፡ ይሁን ፣ ጋብቻውን ፣ ሊያፈርስ ፡ የሚችለው ፡ ጋብቻው ፣ የማይጸና ፣ መሆኑ አግባብ ፣ ባለው ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣን ፡ ሲወሰን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፣ በሌላም ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፡ በታወቀ ፡ ምክንያትም ፡ ነው ፤ ብለን ፣ ብንከራከር ፣ በሃይ ማኖቶች ፣ መካከል ፣ ልዩነት ፡ አይኑር ፣ የሚለውን ፣ አሳብ ፣ በምንም ፡ ረገድ ፡ የሚ ቃረን ፡ አይሆንም ። ቍጥር ፣ ፲፱፻፷፱ም ፣ በትክክል ፡ ይህንኑ ፡ የሚል ፡ ይመስላል ።

(፩) የጋብቻው ፡ ሥርዓት ፣ የተፈጸመበት ፡ ሥርዓት ፡ ማንኛውም ፡ ዐይነት ፣ ቢሆን ፣ የጋብቻው ፣ መፍረስና ፡ ይህ ፣ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ አንድ ፡ ዐይ ነት ፡ ነው ።

(፪) ጋብቻው ፣ የተፈጸመው ፡ በአንድ ፣ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፣ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ ፊት ፣ ወይም ፡ በሃይማኖት ፡ ሥርዓት ፣ ወይም ፣ በአገር ፣ ልማድ ፣ መሠረት ፣ ቢሆን ፣ በጋብቻ ፡ መፍረስ ፣ ረገድ ፣ ማንኛውም ፡ ልዩ ፣ አስ ተያየት ፣ አይደረግም ።

የዚህ ፡ ቍጥር ፣ አነጋገር ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብቻዎችን ፡ መፍረስ ፡ ጉዳይ ፡ ለመ መልከት ፡ የሚችሉት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፣ ባለሥልጣኖች ፣ ብቻ ፡ ናቸው ፣ የሚ ለውን ፣ ሐሳብ ፡ ውድቅ ፣ የሚያደርገው ፣ ይመስላል ። ነገር ፣ ግን ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፣ ሥልጣናችን ፣ የመጣው ፣ አሁንም ፡ የበላይ ፡ ከሆነው ፡ ከሃይ ማኖት ፡ ሕግ ፣ (ከፍትሐ ፡ ነገሥት) ፡ ነው ፡ ይላሉ ። የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፣ ምእመናንን ፡ የሚመራበት ፣ ረቂቅ ፡ ባህርዩ ፡ አለው ፣ በሚለው ፣ በሃይማኖት ፡ መሪዎች ፣ ክርክር ፡ መስማማት ፣ ይገባል ፤ ነገር ፣ ግን ፣ የጋብቻ ፣ መፍረስ ፡ ጉዳይ ፡ ምን ፣ ሕጋዊ ፣ ውጤት ፣ እንዳለው ፡ የሚገልጹት ፡ የመንግሥቱ ፣ ሕጎች ፡ ናቸው ፤ በተጨማሪም ፡ እነዚህ ፣ ሕጎች ፣ የጋብቻ ፣ መፍረስ ፣ ጉዳይ ፣ በዓለማዊ ፡ ባለሥል ጣኖች ፡ ሥልጣን ፣ ስር ፣ እንደሆነ ፡ ይገልጻሉ [19] ።

19. በቍጥር ፣ ፪ ፣ ፲፱፻፴፮ ፣ የተሰጠው ፣ ድንጋጌ ፣ ፲ኛ ፣ አንቀጽ ፣ እና ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፡ ሕግ ፣ ቍጥር ፣ ፲፱፻፶፪ ።

ዳኝነትን ፡ የሚመለከተው ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳይ ፡ ቢወሰንም ፡ ጉዳዩ ፡ በዚሀ ፡ የሚፈጸም ፡ የማይመስለው ፡ መሆኑን ፡ ደራሲው ፡ በአክብሮት ፡ ይገልጻል ። በሱ ፡ አስተያየት ፡ ለዓለማዊና ፡ ለሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተገቢ ፡ ቦታቸውን ፡ በመስጠት ፡ ቍጥር ፡ ፲፻፷፪ን ፡ እና ፡ ፲፻፸፩ን ፡ ማስማማት ፡ ይቻላል ። በዓለማዊ ፡ የሕግ ፡ ቅንጅት ፡ መሠረት ፡ ዓለማዊ ፡ የሕግ ፡ ዝምድና ፡ የሆነውን ፡ ጋብ ቻን ፡ ለማስተዳደር ፡ ዓለማዊ ፡ የሕግ ፡ ቅንጅትና ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከታቸው ፡ ድርጅቶች—ፍርድ ፡ ቤቶች—የበላይ ፡ እንደሆኑ ፡ ቍጥር ፡ ፲፻፷፪ ፡ ይገልጻል ። ይህ ፡ ቍጥር ፡ ሁሉንም ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ ይፈጥራል ፤ በተጨማሪም ፡ ከፍ ተኛው ፡ ድምጽ ፡ የሚደግፈውን ፡ በሃይማኖቶች ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አይደረግ ፡ የሚለውን ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ያጸቁማል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብ ቻን ፡ የፈጸሙ ፡ ሰዎች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ጋብቻቸውን ፡ በመንፈሳዊ ፡ ምክንያ ቶች ፡ ሊያፈርሱ ፡ የሚፈልጉ ፡ መሆናቸው ፤ እነዚሀም ፡ ምክንያቶች ፡ ጥልቅ ፡ ከሆነ ፡ ከሰው ፡ ስሜቶች ፡ ጋር ፡ የተያያዙ ፡ ስለሆኑ ፡ በዓለማዊና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መታወቅ ፡ እንደሚገባቸውና ፡ እነዚህ ፡ ምክንያቶች ፡ መኖር ፡ አለመኖራቸውንም ፡ በደንብ ፡ መወሰን ፡ የሚችሉት ፡ ከዓለማዊ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ይልቅ ፡ መንፈሳዊ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መሆናቸው ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፸፩ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዓለማዊ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ የነበራትን ፡ ሥልጣን ፡ ያስቀረው ፡ ድንጋጌ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ሥል ጣን ፡ እንዳላት ፡ በድጋሚ ፡ ማረጋገጡን ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምእመናንን ፡ በመንፈሳዊ ፡ ረገድ ፡ ተቀባይነት ፡ በሌላቸው ፡ ምክንያቶች ፡ በሕግ ፡ የጸኑ ፡ ፍቺዎች ፡ እንዳያገኙ ፡ ልታደርግ ፡ ካልቻለች ፡ እነዚህን ፡ ለዓለማዊ ፡ ጉዳ ዮች ፡ የጸኑትን ፡ ፍቺዎች ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ጉዳዮችም ፡ የጸኑ ፡ አድርጋ ፡ እንድታ ውቅ ፡ አትገደድም ። ይሀን ፡ ማለት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እነዚህን ፡ ፍቺዎች ፡ "የማይጸኑ" ፡ አድርጋ ፡ ልትቆጥርና ፡ በግል ፡ መንፈሳዊ ፡ ዳኝነቷም ፡ እንደ ፡ አጥፊ ፡ አድርጋ ፡ የምትቆጥራቸውን ፡ ምእመናን ፡ "ልትቀጣ" ፡ ትችላለች ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ፍቺውን ፡ የሚያጸናው ፡ ለዓለማዊ ፡ ጉዳዮች ፡ ቢሆንም ፡ ዓለማ ዊው ፡ ሕግ ፡ ሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ ውሳኔ ፡ አይፈልግም ።

በመጨረሻ ፡ ልንሰጥ ፡ የምንችለው ፡ ማጠቃለያ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ የኢትዮ ጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (ወይም ፡ ሌላ ፡ የሃይማኖት ፡ ድርጅት) ፡ በምእመናን ፡ የጋብቻ ፡ አቋም ፡ ላይ ፡ በነበራት ፡ የበላይነት ፡ ሥልጣን ፡ ፈንታ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ የተተኩ ፡ መሆናቸውን ፡ ነው ፡ የጋብቻን ፡ መፍ ረስ ፡ ጉዳይ ፡ ቍጥር ፡ ፲፻፷፪ ፡ እና ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ ቍጥሮች ፡ ይመለከታሉ ። ተከራካሪዎቹ ፡ ጉዳያቸውን ፡ እቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ፊት ፡ ለማቅ ረብ ፡ ከፈለጉ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጋብቻውን ፡ ለማፍረስ ፡ እሁ ንም ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ። ሆኖም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብቻን ፡ እንዲያፈርሱ ፡ በሚጠየቁ በትም ፡ ጊዜ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ጋብቻው ፡ ለዓለማዊ ፡ ጉዳዮች ፡ መፍረስ ፡ አለመፍ

ረሱን ፡ በማረጋገጥ [20] ፡ የበላይ ፡ ሥልጣን ፡ ወዳላቸው ፡ ወደ ፡ ዓለማዊ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መሄድ ፡ አለባቸው ። ዛሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ በሃይማኖቱ ፡ ሥርዓቶች ፡ መሠረት ፡ ጋብቻ ፡ የፈጸመ ፡ ሰው ፡ (በተመለከትነው ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓቶች ፡ መሠረት) ፡ ለመፋታት ፡ ቢፈለግ ፡ ጋብቻውን ፡ ለማፍረስ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ዓለማዊ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ናቸው ፤ ሊፈርስም ፡ የሚችለው ፡ በዓለማዊ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ነው ። ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በሕጉ ፡ ዓይን ፡ ጋብቻ ፡ ከመንፈሳዊነቱ ፡ ይልቅ ፡ ዓለማዊነቱ ፡ የላቀ ፡ ነው ።

---

20. አንድ ፡ ሰው ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጥያቄ ፡ አቅርቦ ፡ እነርሱም ፡ ውሳኔ ፡ ከሰጡት ፡ ይህ ፡ ውሳኔ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነትን ፡ ካገኘ ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ የጸና ፡ ሆኖ ፡ ይሠራበታል ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ ይቻላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የተያያዙ ፡ ጥያቄዎች ፡ ሕጋዊ ፡ ውሳኔዎችን ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ ወዳላቸው ፡ (ወደ ፡ ተሰጣቸው) ፡ ወደ ፡ ዓለማዊ ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ ፊት ፡ መቅረባቸው ፡ የማይቀር ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ አሁን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እርምጃ ፡ ለመውሰድ ፡ ሕጋዊ ፡ ሥልጣን ፡ አለን ፡ ቢሉም ፡ ወደፊት ፡ ሥልጣናቸው ፡ እየመነመነ ፡ መሄዱ ፡ የማይቀር ፡ ነው ።